
# ጊዜው ፈጥኖ እያለቀ ነው!

## ይህ የቪክቶሪያ ኔህል ምስክርነት አጭር ማጠቃለያ ነው።




የተወለድሁትና መላ ህይወቴን የኖርሁት ናሚቢያ ውስጥ ነው፥ እንዲሁም እ.ኤ.አ በፌብሯሪ 06፥ 2005 ዓ.ም. ህይወቴን ለኢየሱስ ሰጠሁ። **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** ሲያልን ጨምሮ ብዙ በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን ገልጦልኛል። **ጌታ** ገጠመኞቼን ሁሉ ከሰዎች ጋር እንዳካፍል አዞኛል፤ እንዲሁም **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** ካሳየኝ ውስጥ ምንም ነገር እንዳላሳጎድል አልያም እንዳልቀይር አስጠንቅቆኛል። መጽሐፉን በምጽፍበት ጊዜ፥ በ2006 መጨረሻ፥ በ**ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** ለ33 ጊዜ ያህል ተጎብኝቻለሁ። በእነዚያ የጉብኝት ጊዜያቶች ሁሉ፥**ጌታ** ከመሄዱ በፊት እንዲህ ይለኝ ነበር፥

## *ጊዜው ፈጥኖ እያለቀ ነው!*

## ወደ ሲዖል የመጀመሪያው ጉዞ

በጁላይ 23፥2005 በሳምንቱ መጨረሻ፥ከምሠራበትና ከምኖርበት የኦንዳንግዋ ከተማ፥የሳምንቱን መጨረሻ ከቤተሰቦቼ ጋር ለማሳለፍ፥ ወደ ትውልድ ከተማዬ የሠላሳ ደቂቃ የታክሲ ጉዞ አደረግሁ። ወደ ቤት በመሄድ ላይ ሳለሁ፥በዚያ ምሽት ከተለመደው የተለየ የሆነ ነገር እንደሚፈጠር ተሰማኝ። እቤት ከምሽቱ 12:00 ሰዓት አካባቢ ደረስሁ፥ ሰዎች ለእራት የሚዘጋጁበት ሰዓት ነበር። ከቀሪው የቤተሰብ አባላቶቼ ጋር በማድቤት ነበርሁ፥ ወለሉ ላይ በነበረ አሮጌ ምንጣፍ ላይ ጋደም ብዬ፥ የእህቴ/ወንድሜ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ደግሞ የሰንበት ትምህርት ቤት መዝሙሮችን እየዘመሩ። በድንገት ከባድ ቅባት በላዬ ሲወርድ ተሰማኝ፥ ሰውነቴ በጣም ደከመ፥ በ**እግዚአብሔር** ኃይል ስር ሆኜ ተኛሁ። አንድ ሰው እኔ ወደተጋደምሁበት ቦታ ሲመጣ አየሁ፥ ተመሳሳይ ቀለም ባለው ገመድ የታሰረ ረዥም ነጭ ቀሚስ ለብሷል። ልክ ከ**እርሱ** እንደሚፈነጥቅ ደማቅ ብርሃን በዙሪያው አለ። ቡኒ ጥልፍልፍ ጫማ አድርጎ ነበር፤ ገጽታዎቹ በመካከለኛው ምስራቅ እንዳሉ ዓይነት ሰዎች ነበሩ፥ ከሚያምር ጠይም ቆዳ ጋር። ምንም እንኳን ፊቱ ሩኅሩኅና በክብር የተሞላ ቢሆንም እኔ ግን ዓይኑን ላየው አልተቻለኝም። ሲናገር፥ ድምፁ ሞቃት፥ የርኅራኄና የፍቅር ነበር፥ እንደገናም በስልጣን ነበር፤ የፍቅር ሞገዶች ከህልውናው ይመነጩ ነበር።

እጁን ወደ እኔ ዘርግቶ ከተጋደምሁበት ወደ ላይ አነሣኝ። በድንገትም በሚያምር፥ የተለወጠ ሰውነት ውስጥ ነበርሁ፤ የአስራ ስምንት ዓመት ወጣት እያለሁ እንደነበረው እመስል ነበር። በነጭ ገመድ የታሰረ ነጭ ቀሚስ ለብሼ ነበር። ምንም እንኳን ቀሚሱ ነጭ ቢሆንም የተሠራበት ነገር ግን ከሰውየው ቀሚስ የተለየ ነበር። ቀሚሱ ነጸብራቃማ ነበር እኔ ልገልጽው የማልችለው ድንቅ ውበት።

በጣም በፍቅርና በሞቃት ድምፅ፡ “*ቪክቶሪያ፥ ከእኔ ጋር እንድትመጪ እፈልጋለሁ፤ የሚያስፈሩ ነገሮችን አሳይሻለሁ እናም የምወስድሽ ቦታ በህይወት ዘመንሽ ሁሉ ሄደሽበት አታውቂም።*” አለኝ። ቀኝ እጄን ያዘኝና ሄድን። በአየር ላይ እንደምንራመድና ሙሉውን ጊዜ ወደ ላይ እየሄድን እንዳለ ተሰማኝ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በመንገዳችን ላይ፥ እንደደከመኝና ጉዞውን መቀጠል እንደማልችል ነገርሁት እናም ወደ ኋላ ለመመለስ

ለመንሁት። ከዚያም ተመለከተኝና በሚያረጋጋ ድምጽ፡ "*አልደከመሽም - ደህና ነሽ። ከደከመሽ እኔ እሸከምሻለሁ፥ለአሁን ግን ደህና ነሽ። ሰላም ላንቺ ይሁን። እንሂድ።*" አለኝ።

የደረስንበት ቦታ ጭው ያለ በረሃ ነበር፥ ለሰዎች ከታወቁት በረሃዎች ሁሉ የከፋ፥ ምንም ዓይነት ህይወት በየትኛውም መልኩ ፈጽሞ የሌለበት። አንዲት ዛፍ አልያም አንዲት ዘለላ ሣር ወይም ምንም ዓይነት ህይወት ያለው ነገር የለበትም። በእርግጥም በጣም የሚጨንቅ ቦታ ነበር።

ወደ አንድ በር ደረስንና ሰውየው ዞር ብሎ እንዲህ አለኝ፡ "*ቪክቶሪያ፥ በበሮቹ እንገባለን እናም የምታያቸው ነገሮች ሊያስፈሩሽና ሊያናድዱሽ ይችላሉ - ነገር ግን በምወስድሽ ቦታዎች ሁሉ በደንብ እንደምትጠበቂ እርግጠኛ ልትሆኚ ያስፈልጋል። ዓይንሽን ብቻ ክፈቺና የማሳይሽን ሁሉ ተከታተይ።*" በጣም ፈርቼ ነበርና ማልቀስ ጀመርሁ። እየተቃወምሁና ሰውዬው መልሶ እንዲወስደኝ እየለመንሁት ነበር። ወደዚያ ቦታ ለመግባት እንደማልፈልግ ነገርሁት ምክንያቱም በውስጥ እየሆነ ያለውን ነገር በበሩ አሻግሬ ማየት ስለምችል ነው። ወደ እኔ ተመለከተና፡ "*ሰላም ላንቺ ይሁን፤ እኔ ካንቺ ጋር ነኝ። ወደ ውስጥ መግባት ይኖርብናል፥ ምክንያቱም ጊዜው ፈጥኖ እያለቀ ነው።*" አለኝ።

በመግቢያው በኩል ገባን። የዚያን ስፍራ አስፈሪነት ልገልጽላችሁ አልችልም። በመላው ዓለም እንደዚህ ዓይነት አስከፊ ቦታ እንደሌለ አምኛለሁ። ቦታው ከመጠን በላይ ረኀም ነበር እናም በውስጤ በየጊዜው እንደሚያድግ ይሰማኝ ነበር። የድቅድቅ ጨለማ ቦታና ሙቀቱ ሊለካ የማይቻል ነበር፤ ከእሳቶች ሁሉ ሞቃት ከሆነው በላይ ሞቃት ነበር። ምንም ዓይነት የእሣት ነበልባል አልያም ደግሞ የሙቀቱ ምንጭ አይታየኝም ነገር ግን በጣም ሞቃት ነበር። ቦታው ሁሉም ዓይነት መጠን ባላቸው ዝንቦች ተሞልቶ ነበር - አረንጓዴ፥ ጥቁርና ግራጫ ዝንቦች። ሊታሰቡ የሚችሉ ሁሉም ዓይነት ዝንቦች በዚያ ነበሩ። በተጨማሪም፥ አጭር፥ ጠጣር ጥቁር ትሎችም ነበሩ። ትሎቹ ወደ እኛ ላይ መውጣት ጀመሩ እንዲሁም ዝንቦቹ ወረውን ነበር። ቦታው እጅግ አስቀያሚ በሆነ ክርፋት(ግማት) የተሞላ ነበር፤ የዚያን ስፍራ ክርፋት መጠን መግለጫ ቃላት አይገኙም። ሽታው ልክ እንደ በሰበሰ ሥጋ ዓይነት ሆኖ ግን በህይወቴ ዘመን ሁሉ ካሸተትሁት ከከፋው የበሰበሰ ሥጋ መቶ እጥፍ የባሰ ነበር። ቦታው በለቅሶና ጥርስማፋጨት ጩኸት ተሞልቷል፥እንዲሁም ደግሞ የአጋንንት አስቀያሚ ጩኸት።

የዚህ ቦታ አስከፊው ነገር በሰዎች የተሞላ መሆኑ ነው። በጣም ብዙ ሰዎች ከመሆናቸው የተነሳ ሊቆጠሩ አይችሉም። ሰዎቹ በአጽም መልክ ነበሩ። እነዚህ አጽሞች ሰዎች እንደሆኑ በድፍረት መናገር እችላለሁ ምክንያቱም በጣም የቅርብ የሆኑ ዘመዶቼንና የመንደራችንን አንዳንድ ሰዎች አይቻለሁ። አጥንቶቻቸው ጥቁር ግራጫ ሆኖ ከመጠን በላይ ደረቅ ነው። ልክ እንደ አውሬ ረኀም ስለታም ጥርሶች ነበሯቸው። አፋቸው ትልቅ ሆኖ ሰፊ ሲሆን ምላሳቸው ደግሞ ረኀምና ፈካ ያላ ቀይ ቀለም ነበረው። እጆቻቸውና እግሮቻቸው፥ ረዣዥም ስለታም ጥፍሮች ያሏቸው ቀጫጭን ጣቶች ነበራቸው። አንዳንዶቹ ጭራና ቀንዶችም ነበራቸው።

ከሰዎቹ ጋር የተደባለቁ አጋንንት ነበሩ፤ አጋንንቶቹ ገጽታቸው እንደ አዞ ሲሆን በአራት እግራቸውም ይራመዱ ነበር። ያ ቦታ ተመችቷቸው ነበር እናም ሰዎቹን በተደጋጋሚ ያሾፉባቸውና ያሰቃዩአቸው ነበር። አጋንንቶቹ የሚያወጡት ድምጽ የፌሽታ ዓይነት ነበር፥ ደስተኛና የማይጨነቁ ይመስላሉ፤ እንዲሁም በሁሉም ጊዜ ይደንሱና ይዘሉ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎቹ፥ የተመሰቃቀሉና የተከዙ ይመስሉ ነበር፤ እርዳታ ቢሶችና በተስፋ መቁረጥ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ። ከሰዎቹ የሚወጡት ድምጾች ከህመም የተነሳ ነበሩ፤ ያለቅሱ፥ ይጮኹና ጥርሳቸውን ያፋጩ ነበር፥ እንዲሁም በማይታሰብ ህመምና ስቃይ ባለበት አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ።

በዚህ ቦታ ያሉት ሰዎች የማይቆጠሩ ናቸው፥ ሆኖም ግን አብዛኞቹ ሴቶች ነበሩ። በተለያዩ ብዙ ቡድኖች ተከፋፍለው ነበር። ምንም እንኳን በቡድን ቢሆኑም ከብዛታቸው የተነሳ በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ያሉትን ሰዎች ቁጥር ለማወቅ አይቻልም።

ሰውዬው በምስራቅ በኩል ወዳሉት ቡድኖች ወሰደኝ፡ ተመለከተኝና "*ቪክቶሪያ፥ እነዚህ ቡድኖች ሌሎችን ይቅር ለማለት ያልቻሉ ሰዎች ናቸው። ብዙ ጊዜ በተለያየ መንገድ ሌሎችን ይቅር እንዲሉ ነግሬያቸው ነበር ነገር ግን እንቢ አሉኝ፤ እኔ ሁሉንም ይቅር ብያቸዋለሁ ነገር ግን እነርሱ ሌሎችን ይቅር ሊሉ አልቻሉም። ጊዜያቸው አለቀና ራሳቸውን በዚህ አገኙት። ለዘላለም በዚህ ይሆናሉ፤ ከዘላለም እስከዘላለም የድካማቸውን ፍሬ ይበላሉ። ሆኖም ግን፥ እነርሱን በዚህ አስከፊ ቦታና ዘላለማዊ ሁኔታ ውስጥ ማየት ለእኔ በጣም የሚያሳምመኝ ነው - ምክንያቱም ስለምወዳቸው።*" አለኝ።

ከዚያም ወደሚቀጥለው ቡድን ተመራሁ፥ እናም ሰውየው በዚህ ሁለተኛው ቡድን ውስጥ ያሉት ሰዎች እዳ ያለባቸው ሰዎች እንደሆኑ ነገረኝ። በዚያ ቡድን ውስጥ ሦስት ዓይነት ክፍፍሎች ነበሩ። የመጀመሪያው ክፍል የሌላ ሰው እዳ ያለባቸው ናቸው፤ እዳቸውን የመክፈል አቅም ነበራቸው ግን በተደጋጋሚ ያስተላልፉትና ያራዝሙት ነበር። ጊዜው እስኪያልቅባቸው ድረስ ነገ፥ በሚቀጥለው ሳምንት፥ በሚቀጥለው አመት እንደሚከፍሉ ይናገሩ ነበር እናም አሁን ራሳቸውን በዚህ ስፍራ አገኙት። ይህ ለዘላለም የሚሆኑበት ቦታ ነው፤ የድካማቸውን ፍሬ እየበሉ ነው።

ሁለተኞቹ ክፍሎች ደግሞ እዳቸውን የመክፈል አቅም ያላቸውና እዳቸውንም ለመክፈል ፈቃደኛ የሆኑ ናቸው፥ ነገር ግን ቀጥሎ የሚከሰተውን ነገር ይፈራሉ ምክንያቱም፥ ምንአልባትም፥ እውነቱን ቢናገሩ መገለል ሊደርስባቸው ይችላል አልያም እስር ቤት ሊገቡ ይችላሉ ወይም ደግሞ የሠሩት ሥራ ለመላው ዓለም ይፋ ሊሆንና ሊዋረዱ ይችላሉ። ሰውየው እንዲህ አለኝ፡ "*አንዳቸውም መንገዱን ፍለጋ ወደ እኔ አልመጡም። እንደዚያ ቢያደርጉ ኖሮ፥ ቀላሉን መውጫ መንገድ ባሳየኋቸው ነበር። በማንኛውም መንገድ ሊረዳቸው ያልቻለውን የራሳቸውን መንገድና አስተሳሰብ መረጡ። ጊዜያቸው አለቀና ራሳቸውን ለዘላለም በሚሆኑበት በዚህ ስፍራ አገኙት። የድካማቸውን ፍሬ እየበሉ ነው።*"

እንዲህ አለኝ፡ "*ሦስተኛው ክፍል፥ ሊከፍሉት የማይችሉት እዳ ነበረባቸው፥ ነገር ግን፥ አሁንም፥ አንዳቸውም ሊከፍሉት የማይችሉት እዳ እንዳለባቸው አልነገሩኝም። እንደዛ አድርገው ቢሆን ኖሮ፥ እኔ እዳቸውን በከፈልሁላቸው ነበር። እነርሱም ደግሞ የራሳቸውን አስተሳሰብና ጥበብ መረጡ፥ በማንኛውም መንገድ አልጠቀማቸውም። እናም አሁን ራሳቸውን ሁሉጊዜ በሚሆኑበት በዚህ ስፍራ አገኙት። የድካማቸውን ፍሬ እየበሉ ነው። እጅግ በጣም ስለምወዳቸው ስለነዚህ ሁሉ ሰዎች ልቤ ይታመማል።*"

በመጀመሪያው ምድብ፥ ሁለት የቅርብ ሴት ዘመዶቼን አየሁ፥ እንዲሁም አንዲት ባለ አስራ ሁለት ዓመት፥ እንዲሁ የቅርብ ዘመዴ። አስራሁለት ዓመቷ እንደሆነ ያወቅሁት የሞተችው በአስራሁለት ዓመት እድሜዋ ስለሆነ ነው። በሁለተኛውም ምድብ እንዲሁ ዘመዶቼን አየሁ፥ እንዲሁም በደንብ የማውቀው መጋቢ(ፓስተር)። ጃክስ፥ እኔ ህይወቴን **ለክርስቶስ** በመስጠቴ ምክንያት ራሱን ያጠፋው የወንድ ጓደኛዬ፥ እርሱም በሁለተኛው ምድብ ውስጥ ነበር። በሁለቱም ምድቦች ውስጥ አንዳንድ ጎረቤቶቼን እንዲሁ አይቻለሁ።

ከመሞታቸው ቢፊት የማውቃቸውን ሰዎች በዚያ አወቅኋቸው፤ እነርሱም አውቀውኛል። ዘመዶቼ ሲያዩኝ በጣም ተናደውብኝ ነበር እናም ክብር የሚነኩ ቃላትን ይናገሩኝ ጀመር፤ ሲሰድቡኝ በጣም አስጸያፊ የሆኑ ቃላትን ይጠቀሙ ነበር። አንደኛዋ አብሬው ያለውን **ሰው** ልከተለው የሚገባኝ እንዳልሆነ ነገረችኝ፤ ህይወቴን **ለክርስቶስ** ከመስጠቴ በፊት ሳደርጋቸው የነበሩትን ነገሮች ይናገሩ ነበር። እየዋሹ አልነበረም፤ እኔን እየከሰሱባቸው የነበሩት ነገሮች እውነት ነበሩ። ጃክስ እያለ የነበረው የእርሱ እንደነበርሁና እርሱ ያደርጋቸው የነበሩትን ኃጢአቶች እፈጽም ስለነበር እርሱ(ጃክስ) ያለበት ቦታ ልሆን እንደሚገባ ነው። መጋቢው በመጀመሪያ ሲያየኝ ደስተኛ ይመስል ነበር እናም በመምጣቴ ጥሩ እንዳደረግሁ ነገረኝ ነገር ግን አብሮኝ የነበረውን ባየ ጊዜ ሁኔታው ሁሉ ተለወጠ እናም እርሱም(መጋቢውም) ስድቡንና ክብር የሚነካ ንግግሩን ተቀላቀለ። አብሮኝ ያለው ሰው የሚያደርጉትን ስለማያውቁ ችላ እንድላቸው ነገረኝ።

ደንግጬና በጣም አዝኜ ነበር፤ ሰውነቴ እየተንቀጠቀጠና መቆም ተስኖኝ ነበር። ከቁጥጥር በላይ እያለቀስሁ ነበር። ሰውየው ወደ እኔ ዞረ፥ አቀፈኝና፥ "*ሰላም ላንቺ ይሁን፥ ቪክቶሪያ፤*" አለኝ። ብርታቴ ተመለሰልኝና በእቅፉ ውስጥ ጥበቃ ተሰማኝ። ከዚያም ቦታውን ለቅቀን መመለስ እንዳለብን ነገረኝ። ወደ እኔ ተመለከተና እንዲህ አለ፡ "*ቪክቶሪያ፥አሳይቼሻለሁ። አሁን በየትኛው ምድብ መሆን እንደምትፈልጊ መምረጥ ይኖርብሻል፤ ምርጫው በራስሽ እጅ ውስጥ ነው። ያየሽውንና ያሳለፍሽውን ሁሉ ለሰዎች መንገር ይኖርብሻል ነገር ግን ምንም መጨመር ወይም መቀየር አትችይም።*"

ከዚያ አስከፊ የሆነ ቦታ ለቅቀን ስንወጣ አስታውሳለሁ ነገር ግን **እርሱን** የት እንደተውሁት አላውቅም ምክንያቱም ስነቃ፥ ዓይኖቼን ከፈትሁ እናም ወደ ሥጋዊ አካሌ ተመልሻለሁ፥ በኦሻካቲ ሆኪምቤት (Oshakati Hospital) ውስጥ ተኝቼ። በግራ እጄ ላይ ጉልኮስ ተሰክቶ ነበር፥ እንዲሁም ቤተሰቦቼንና ከመንደራችን አንዳንድ ጎረቤቶቼን በክፍሉ ሌላኛው ጥግ አየኋቸው፥ በመደነቅ እየተመለከቱኝ ነበር። እናቴ እያለቀሰች እንደነበረ ከፊቷ ላይ ማየት እችል ነበር። በእኔ ምን ችግር እንደተከሰተብኝ እንድትነግረኝ አንዷን ነርስ ጠየቅኋት ነገር ግን እየቀለደችብኝ "*ተመልሰሽ ተልከሻል፤ ምን አልባት አንድ ነገር አጥፍተሻልና ንስሐ ልትገቢ ሳያስፈልግሽ አይቀርም።*" አለችኝ። ነርሷ ስለእኔ ሁኔታ ቀለል አድርጋ ለመናገር እየሞከረች ነበር ነገር ግን ወደ እኔ መቅረብ እንደፈራች ማየት እችል ነበር። የተከታተለኝን ሀኪም እንድትጠራው ጠየቅኋት።

(ሀኪሙ) እንደመጣ፥ የእኔ ችግር ምን እንደሆነ እንዳላወቀ ነገረኝ። በመጀመሪያ፥ ወባ የያዘኝ መስሎት ነበር ነገር ግን የምርመራ ውጤቱ ነፃ ሆነ። ከዚያም የሰውነት ሙቀቴ፥ የልብ ምቴና የደም ግፊቴ በአደገኛ ሁኔታ ዝቅተኛ እንደነበረ ነገር ግን ችግሬ ምን እንደሆነ ለማወቅ እንዳልቻለ መናገሩን ቀጠለ። ምንም ሊያደርግልኝ የሚችለው ነገር እንዳልነበረ ነገረኝ፤ ታምሜ ስላልነበር ሊያክመኝ አልቻለም። ያደረጉልኝ ጠብታ (ጉልኮስ) በመጀመሪያ እየሠራ አልነበረም ነገር ግን ዓይኖቼን ስከፍት፥ መሥራት ጀመረ። ወደ ቤት ለመሄድ ብርታት እንዳገኝ ነርሷ የመጀመሪያው ጠብታ (ጉልኮስ) እንዳለቀ ሌላ እንድትሰጠኝ መከረ።

በዚያ ስፍራ ባየሁት ነገር በጣም ፈርቼ ስለነበር ማልቀሴን ላቆም አልቻልሁም። የቦታው ክርፋት ነቅቼ ራሱ እዛው ያለው ያህል ያለማቋረጥ እውን ሆኖ ይሰማኛል። ከስፍራው ያየሁት እይታ ሁልጊዜ ከፊቴ ድቅን ይላል። መተኛት አልቻልሁም እናም ሰውነቴ ደግሞ በከባድ ህመም ውስጥ ነበር። መገጣጠሚያዎቼ ሁሉ ወላልቀው እንደገና የተገጣጠሙ ያህል ነው የተሰማኝ፥ ቅፍፍ አለኝ። ሳምንቱን ሙሉ ተቅማጥና ራስምታት ይሰማኝ ነበር።

ስላየሁት ነገር ለማንም እንዳላወራ በአዕምሮዬ ወስኜ ነበር ምክንያቱም ማን ሊያምነኝ ይችላል? ሰዎች ምን ሊያስቡ ይችላሉ? ያሳለፍሁትን ከማንም ጋር ላላነጻጽር ለራሴ ደጋገሜ መናገሬን ቀጠልሁበት። ከአማካሪዎቼ አንዷ እንድትጸልይልኝ የስልክ መልእክት ልኬላት ስለነበር ስለጤንነቴ ለመጠየቅ ደወለችልኝ። ሳላውቀው ስለገጠመኝ እየነገርኋት ነበር። ምን እያደረግሁ እንደሆነ ባስተዋልሁበት ጊዜ አብዛኛውን ታሪክ ነግሬያት ነበር። ራሴን ለመምታት ፈለግሁ። በህይወቴ ውስጥ ከባዱን ስህተት እንደሠራሁ አምኜ ስለነበር እያለቀስሁ ነበር። አሁን ታሪኩ ተነግሯል፥ ከእንግዲህ ወዲያ ልደብቀው የሚያስችለኝ ምንም ዓይነት መንገድ የለም። አሁን አንድ ነገር ተረዳሁ፥ **እግዚአብሔር** አንድ ነገር እንዲነገር ከፈለገ፥ ይነገራል። ዞሮ ዞሮ፥ **እርሱ አምላክ** ነው።

በኦገስት 19፥ (**የእግዚአብሔር**) የቅባቱ ምልክቶች በላዬ ላይ እየተሰሙኝ ነቃሁ። ደክሜና እየተንቀጠቀጥሁ ነበር፥ የኤሌክትሪክ ሞገዶች በሰውነቴ ውስጥ ይሄዳሉ። ምሽት ላይ ደማቅ ብርሃን ወደ ክፍሉ ሲመጣ አየሁ እናም በመካከሉ ያ ሰው ራሱ ነበር። በዚህ ጊዜ ከአልጋዬ አጠገብ በወንበር ላይ ተቀመጠ። ይህ ወንበር ከየት እንደመጣ አላውቅም ነገር ግን ለመቀመጥ እንደተዘጋጀ ወንበሩ ቀድሞ ተዘጋጅቷል። ከሙሉ ወርቅ የተሠራ የሚያምር ወንበር ነበር፤ ቅርጹ እንደማንኛውም ዓይነት ወንበር ነበር፥ከኋላው ባለመደገፊያ። ሁሉም እግሮቹ

ላይ ወርቅ ያለበት ብርማ ኮከብ ነበረበት፤ ተመሳሳይ ኮከብ በኋላ መደገፊያው መሐል ላይም ይገኝ ነበር። እያንዳንዱ እግር ላይ ክብ ጎማዎች ነበሩ።

ሰላምታ ከሰጠኝ በኋላ፥ ስለማንነቱ ብዙ ጥያቄዎች እንዳሉኝ እንደሚያውቅና ራሱን ሊገልጥልኝና ስላሳየኝ ነገሮች አንዳንድ ነገሮችን ሊያብራራልኝ እንደመጣ ነገረኝ። እንዲህ አለ፡ "*እኔ ክርስቶስ ነኝ፥ አዳኝሽ። አንዳች ከተጠራጠርሽ እጆቼን ተመልከቺ። የሄድንበት ቦታ ሲዖል ይባላል።*" እጆቹን ስመለከት ሚስማሮቹ የወጉትን ቀዳዳዎች አየሁ።

ውድ ወዳጆች፥ ሲዖል የማንም ሰው የምናብ ፈጠራ እንዳልሆነ እንድትረዱ እፈልጋለሁ ነገር ግን እውነት የሆነና አስቀያሚ ነው። ለሰዎች አልነበረም የተሠራው ነገር ግን ለሰይጣንና ለአጋንንቶቹ ነው። የእኛ ትክክለኛ ቦታችን በገነት ከ**ኢየሱስ** ጋር ነው ቢሆንም ግን ከመርፈዱ በፊት **ኢየሱስን** ልንመርጥ ያስፈልገናል። ዛሬ፥ ድምፁን ስትሰሙ ልባችሁን አታጽኑ፤ **ኢየሱስን** እንደ የግል አዳኛችሁ አድርጋችሁ ተቀበሉትና ለ**እርሱ** ኑሩ። ሲዖል አስከፊ ቦታ ነው፤ የፍርሃትና የሐዘን ቦታ ነው፤ የሥቃይና የዘላለም ዋይታ እንዲሁም የጥርስ ማፋጨት ቦታ ነው። ሰይጣን የሚችለውን ያህል ሰው ከእርሱ ጋር መውሰድ ይፈልጋል። ከ*እርሱ(ከሰይጣን)* ጋር አትተባበሩ፤ ከ**ኢየሱስ** ጋር ተባበሩና በሕይወት ትኖራላችሁ እንጂ አትሞቱም።

**ጌታ** ዳግም የተወለድሁ ክርስቲያን ሆኜ ሳለ በሲዖል ካሳየኝ ከሁለቱ ምድቦች አንዱን እንድመርጥ ለምን እንደነገረኝ ልረዳው አልቻልሁም። ወደ ህይወቴ ተቀብዬዋለው ሆኖም ግን አሁንም ሲዖል መሄድ እንደምፈልግና እንደማልፈልግ እንድወስን ይነግረኛል። ልረዳው አልቻልሁም። ወደ **እግዚአብሔር** በመጸለይ ምን ለማለት እንደፈለገና ምን እንዳደርግ እንደሚፈልግ ጠየቅሁት። *ጌታ በአንደኛዋ እህቴ ላይና በአክስቴ ልጅ ላይ በልቤ ቂምና ክፋት እንዳለ ገለጠልኝ* **ጌታን** ይቅር ስለማይለው መንፈሴ ይቅር እንዲለኝ ጠየቅሁት፤ እንዲሁም እህቴን ቂምና ክፋት በልቤ ስለያዝሁባት ይቅር እንድትለኝ ጠየቅኋት። *ጌታም ሂጂ ከአክስቴ ልጅ ይቅርታ እንድጠይቅ አዘዘኝ።*

*ጌታ አንድ ጊዜ በተጭበረበረ ዲፕሎማ የአስተማሪነት ሥራ እንደ ተቀጠርሁና እርሱም ያን እንደ እዳና እንደ ወንጀል እንደሚቆጥረው ነገረኝ።* ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ወስኜ ነበርና **ጌታን** በዚህ ችግር ውስጥ እንዲረዳኝና ቀላሉን መውጫ መንገድ እንዲያሳየኝ ጠየቅሁት ምክንያቱም ይህ እስር ቤት ሊያስገባኝ የሚችል ከባድ ወንጀል ነበር። ወደ ትምህርት ክፍል ሄጄ ያደረግሁትን እንድናዘዝ ነገረኝ። የማይቀር ከሆነ ወደ እስር ቤት ለመሄድ ዝግጁ ነበርሁ። የ**ጌታ** ሞገስ በትልቁ መንገድ ሆነልኝ። የትምህርት ክፍሉ ሀላፊዎች ምን ማድረግ እንዳለብኝ እንድወስን ነገሩኝ፤ የተቀበልሁትን ደሞዝ ለመንግሥት እንደምከፍል ወይም እንደማልከፍል። ጥፋቴን በመናዘዜ ስለተደነቁ ክስ እንደማይመሰርቱብኝ ቃል ገቡልኝ። አምላካችን **ቃሉን** የሚያከብር ታማኝ **አምላክ** ነው።

እኔ እንደነበርሁበት ዓይነት ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ከሆነ ያላችሁት፥ ትክክለኛ የሆነውን ነገር እንድታደርጉ ላበረታታችሁ እወዳለሁ፥ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን። በምድራዊ እስር ቤት ውስጥ ሊዘጋባችሁ ይችላል ነገር ግን ያ ጊዜያዊ ነው። ማንኛውም ሀፍረትና ህመም ለዘላለም ከ**እግዚአብሔር** ጋር ተለይቶ ከመኖር ጋር ሊወዳደር አይችልም። ሲዖል ጥሩ ቦታ አይደለም፤ ከመርፈዱ በፊት **እግዚአብሔርን** አሁን እንዲፈርድባችሁ መፍቀድ ይሻላል። በጸጋ ጊዜ ውስጥ ሆነን የ**እግዚአብሐርን** ፍርድ ልንፈራ አይገባም፤ በህይወታችን ውስጥ ያለውን ማንኛውም ስህተት ከ**እርሱ** ጋር ራሳችንን ማስተካከያ ጊዜ ባለን በአሁኑ ሰዓት እንዲገልጠው ልንፈቅድለት ይገባል ምክንያቱም ከመቃብር ባሻገር ይቅርታ የለም።

## 2ኛ ጉዞ ወደ ሲዖል

በኦክቶበር 18፥2005 ጧት 11:30 ላይ ከእንቅልፌ ነቃሁ ሆኖም ግን ሥራ ለመሄድ አልቻልሁም። በጣም ድካምና ስካር ተሰምቶኝ ነበር፤ በአልጋዬ ላይ መንቀሳቀስም ሆነ መገላበጥ አልቻልሁም፥ እንዲሁም የ**ጌታ**

ህልውና በክፍሉ በኃይል ነበር። እየተንቀጠቀጥሁ ነበር እናም የኤሌክትሪክ ንዝረት በሰውነቴ ውስጥ ሲሄድ ይሰማኝ ነበር። **ጌታ** ሊወስደኝ የመጣው ከ2:00 በፊት ነበር ምክንያቱም ለመጨረሻ ጊዜ ሰዓቴን ያየሁት 1:48 ላይ ነበር፥ እናም **እርሱ** ከዚያ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነበር የመጣው። ሰላምታ ከሰጠኝ በኋላ ደግመን ተመልሰን መሄድ እንዳለብን ነገረኝ ምክንያቱም ጊዜው ፈጥኖ እያለቀ ነው። ተነሣሁኝና መሄድ ጀመርን። ዛሬ እየሄድንበት ያለው መንገድ ከእስከዛሬዎቹ መንገዶች በጣም የተለየ ነበር፤ ምንም እንኳን እግራችን እንደሚራመድ ቢሆንም ጉዟችን ግን ከመራመድ ይልቅ እንደ መንሳፈፍ ነው። በመንገድ ሳለን፥ ***ኢየሱስ** ሁሉም ኃጢአቶች አንድ እንደሆኑና ትንሽ ወይም ትልቅ የሚባል ኃጢአት እንደሌለ ነገረኝ። ሁሉም ኃጢአት ወደ ሞት ነው የሚያመራው፥ የፈለገ ትልቅ ወይም ትንሽ ቢሆን። **ጌታ** ሲያልን ለመጎብኘት እንደምንሄድ ነግሮኝ ፈርቼ እንደሆነ ጠየቀኝ።*እንደፈራሁ መለስሁለት።

እንዲህ አለኝ: “***የፍርሀት መንፈስ ከእኔም ሆነ ከአባቴ አይደለም፥ ነገር ግን ከሰይጣን ነው። ፍርሀት ወደ ሲያል የሚያደርስሽን ነገር እንድታደርጊ ያደርግሻል።***”

ያለ እምነት **እግዚአብሔርን** ደስ ማሰኘት አይቻልም ፍርኃት ደግሞ የእምነት ቀጥተኛ ተቃራኒ ነው። ፍርኃት **እግዚአብሔርን** ደስ እንደማያሰኘው ግልጽ ነው ምክንያቱም የአንድን ሰው እምነት ስለሚያጠፋ ነው። ሙሉውን ጊዜ በመንገድ ላይ ነበርን፥ ጎን ለጎን እየሄድን ነበር ነገር ግን ልክ ከሲያል ደጃፍ እንደደረስን፥ እጄን በእጁ ያዘኝ እናም እያንዳንዷን በሲያል የቆየንባትን ጊዜ እጄን ይዞኝ ነበር። **ጌታ** እጄን ስለያዘው ደስ ብሎኝ ነበር ምክንያቱም ፈርጣማው አያያዙ ፍርኃትን ሁሉ ከውስጤ አስወግዶት ነበር። ስፍራው አሁንም እንደዛው ነው፤ ከመጀመሪያው ጊዜ ምንም የተለወጠ ነገር የለም። ዝንቦች፣ ትሎች፣ ከባድ ሙቀት፣ ሽታው፣ አጽሞቹ፣ ጫጫታው ነበረ፤ ሀሉም ነገር መጀመሪያ ጊዜ በእዚያ ሳለሁ እንደነበረው እንደዚያው ነበር። በዛው አስቀያሚ በር ገባንና **ጌታ** በህብረት ወዳሉ ሰዎች ወሰደኝ። በምድር ላይ በህይወት ሳሉ የማውቃቸው ብዙ ሰዎች ነበሩ። ምስኪኖቹ ሰዎች በአስከፊ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ፤ የተመሰቃቀሉና በሰቆቃ ውስጥ ያሉ ይመስላሉ ነገር ግን የባሰው ነገር በፊታቸው ላይ የሚታየው ተስፋ መቁረጥ ነው።

**ጌታ** ከመሞቷ በፊት የማውቃት አንድ መካከለኛ እድሜ ላይ ያለችን ሴት ጠቆመ። በ2005 መጀመሪያ ላይ ነበር በመኪና አደጋ የሞተችው። ያቺን ሴት በሲያል በማየቴ በጣም ነበር የደነገጥሁት ምክንያቱም **እግዚአብሔርን** የምትፈራና **እግዚአብሔርን** የምትወድ እንደሆነች ነው ሁላችንም የምናውቀው። ***ጌታ** ያቺ ሴት ትወደው እንደነበረና **እርሱም** ይወዳት እንደነበረ ነገረኝ፤ በምድር ሳለች አገልግላዋለች፤ ብዙ ሰዎችን ወደ **ጌታ** መርታለች እናም ቃሉን በደንብ ታውቃለች። ለድሆችና ለችግረኞች የምትራራ ነበረች፤ ትሰጣቸውና በብዙ መልኩ ትረዳቸው ነበር። በብዙ መልኩ መልካም የ**ጌታ** አገልጋይ ነበረች።*

እነዚህ የ**ጌታ** ቃላት የባሰ አስደነገጡኝ እናም እንዴት እንደዚህ በመልካም ያገለገለውን ሰው በሲያል እንዲጣል እንደሚፈቅድ ጠየቅሁት። **ጌታም** ተመለከተኝና ይህች ሴት የሰይጣንን ማታለል እንዳመነች ነገረኝ። ምንም እንኳን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በደንብ ብታውቅም፥ ትልቅና ትንሽ ኃጢአቶች አሉ የሚለውን የሰይጣንን ማታለል አመነች። ‘ትንሽ’ ኃጢአት ወደ ሲያል እንደማይወስዳት አሰበች፥ ምክንያቱም፥ ምንም ቢሆን፥ ክርስቲያን ስለሆነች።

**ጌታም** ቀጠለ: “***በተደጋጋሚ ወደ እርሷ ሄጄ የምታደርገውን እንድታቆም ነገርኳት ነገር ግን የምታደርገው ነገር ትንሽ እንደሆነ ታሳብ ነበር እናም ማስጠንቀቂያዬን እንደራሷ የጥፋተኝነት ስሜት ቆጠረችው። ለሆነ ጊዜ ያህል ያቆመችበት ወቅት ነበር ነገር ግን ማስጠንቀቂያዎቹ ከእኔ ሳይሆን የራሷ ድምፅ እንደሆነ እራሷን አሳመነች ምክንያቱም ያ ኃጢአት መንፈስ ቅዱስን ለማሳዘን ትንሽ እንደሆነ ስላሰበች።***”

**ጌታን** የዚህች ሴት ኃጢአት ምን እንደሆነ እንዲነግረኝ በድጋሚ ጠየቅሁት እናም ይህን መለሰልኝ: “***ይህች ሴት ኦሻካቲ ሆስፒታል ውስጥ የምትሠራ ነርስ ጓደኛ ነበረቻት። በታመመች ጊዜ ሁሉ፥ ሄዳ እንደአግባቡ የሆስፒታል ካርድ አታወጣም፤ ስልኳን አንስታ ለጓደኛዋ ከሆስፒታል መጋዘን ውስጥ መድኃኒት***

*እንድታዘጋጅላት ትነግራታለች። ጓደኛዋ ሁል ጊዜ ትታዘዛትና የሆነ ሰዓት መጥታ መድኃኒቶቹን እንድትወስድ ትነግራታለች። በመጀመሪያ፥ የሰይጣንን የትንሽና ትልቅ ኃጢአት ውሸት ለማመንና የእኔን እውነት ለመተው ወሰነች፤ ሌላ ሰው በእርሷ ፋንታ ኃጢአት እንዲሠራና እንዲሰርቅ አደረገች ነገር ግን ከሁሉ የሚከፋው፥ መንፈስ ቅዱስን አሳዘነች። ወደ ሲዖል እንድትገባ ያደረጋት ይህ ነው። ሚሊየን ነፍሳትን እንኳ ወደ ጌታ ብታመጡ ለውጥ የለውም፤ መንፈስ ቅዱስን በማሳዘናችሁ ወደ ሲዖል ልትወርዱ ትችላላችሁ። ስለሌሎች ነፍሳት መዳን ብቻ አይደለም ማሰብ ያለባችሁ ነገር ግን የራሳችሁንም ነፍስ እንዳትረሱ ልትጠነቀቁ ይገባል። በሁሉም ጊዜ ለመንፈስ ቅዱስ ንቁ ሁኑ።(Be sensitive to the Holy Spirit at all times.)*" **ጌታ** እነዚህን ቃላት ከተናገረ በኋላ *መመለስ አለብን* አለኝ።

ይህን ታሪክ የሰሙ ብዙ ክርስቲያኖች አዳጋች ሆኖ ያገኙታል። ሁልጊዜም ይጠይቁኛል፡ "*ታዲያ መጽደቅ፥ ምህረትና ጸጋስ?*" እና "*ድኅነትን ከተቀበሉ በኋላ ሊታጣ ይችላል ማለት ነው?*" "*ትንሽ አልጠነከረም?*" "***እግዚአብሔር** እንደዚህ ጨካኝ ሊሆን ይችላል?*"

እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ ላይ በሌላ ቦታ እንደተናገርሁት፥ ምንም ዓይነት ቲዎሎጂ (መንፈሳዊ ትምህርት፣ የስነ-መለኮት ትምህርት) እያቀረብሁ አይደለም። **ጌታ** ያሳየኝንና ያስተማረኝን ነገር ብቻ ነው እየነገርኋችሁ ያለሁት - እንዲሁም እንዳየው የፈቀደልኝን ነገር። እባካችሁ ለመልሳችሁ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አመሳክሩ። እነዚህን ጥቅሶች ተመልከቱና የራሳችሁን ፍርድ ፍረዱ።

*ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ። (1ቆሮንቶስ 9:27)*

*እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? (ሮሜ 6:1-2)*

*እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፤ (ሮሜ.6:12)*

*የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና፥ የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ። (ዕብራውያን 10:26-27)*

**ጌታን** ካገለገልሁና ብዙ ሰዎችን ወደ **ክርስቶስ** ከመራሁ በኋላ ወደ ሲዖል ልወርድ እችላለሁን? እናንተው ፍረዱ!

## አለመታዘዝ

ማርች 6፥2006 ሰኞ እለት፥ በሰዓቱ ጨኸት (አላርም) 11:30 (05H30) ላይ ነቃሁ። መጸለይ ጀመርሁና በላዬ ላይ ከባድ ቅባት እንዳለ አስተዋልሁ። ሰውነቴ በጣም ዝሎ እየተንገዳገድሁ ነበር፤ የኤሌክትሪክ ሞገድ በሰውነቴ ውስጥ እያለፈ ነበር።

ከሰዓት ላይ፥ አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ ሳለ፥ ደማቅ ብርሃን ክፍሉን ሲሞላ አየሁ። የስፒል ጫፍ የሚያካክሉ ትናንሽ፣ ነጫጭ ክብ ድቡልቡል ነጠብጣቦች ሲወርዱ አየሁ። ነጠብጣቦቹ እንደ ዝናብ ይወርዱና በነኩኝ ጊዜ ወደ ሰውነቴ ውስጥ ይሰጥሙ ነበር። በተጨማሪም፥ እንደ ደመና ዓይነት ነጭ ጉም ከላይ ሲወርድ ይታየኛል፤ ይህም ክፍሉን ሞላውና በነካኝ ጊዜ ወደ ሰውነቴ ይሰርግ ነበር። ከዚህ በኋላ፥ **ኢየሱስ** በደመናው

ጉም መሀል ወደ እኔ ሲመጣ አየሁት። በወንበሩ ላይ ከአልጋዬ አጠገብ ተቀመጠ። ይህ ወንበር ከየት እንደሚመጣ አላውቅም፤ ሁል ጊዜም እርሱ ለመቀመጥ ሲዘጋጅ ነው የሚመጣው። ከድፍን ወርቅ የተሠራ የተዋበ ወንበር ነው። ወንበሩ እንደማንኛውም ዓይነት ወንበር ሆኖ የጀርባ መደገፊያ አለው። እያንዳንዱ እግር ላይ የብር ኮከቦች አሉበት፤ ተመሳሳይ ሆኖ ነገር ግን ትልቅ ኮከብ በመደገፊያው ላይ አለ። ሁሉም እግሮች ላይ ክብ ጎማዎች አሉት።

ኢየሱስ ሰላምታ ሰጠኝና እጁን ዘርግቶልኝ እንድነሳ ነገረኝ ምክንያቱም ጊዜው በፍጥነት እያለቀ ነው። እጄን ይዞ ቀና አደረገኝና አልጋዬ ላይ ቁጭ አልኩኝ።

ከዚያም እንዲህ አለኝ፡ "*ቪክቶሪያ፥ እስቲ እንጸልይ።*" እኔ ባልተረዳሁት ቋንቋ ጸለየ፤ 'አሜን' የሚለውን ቃል ብቻ ነበር የተረዳሁት። ከዚያም *ምን ታያለሽ* ብሎ በመጠየቅ ቀጠለ እናም ሰዎች ወደ ሥራ ቦታቸው ሲሄዱና አንዳንዶች ወደ ሥራ ቦታቸው ሲደርሱ አያለሁ አልሁት። እንዲሁም እነዚህ ትናንሽ ጠብታዎች በሥራ ገበታቸው ላይ ቀድመው በሚገኙት ላይ ሲያርፉ አየሁ። ከመጀመሪያዎቹ ሰዎች በኋላ ሌሎች ደግሞ በኋላ ላይ መጡ በዚያ ጊዜ የሚዘንቡት ነጠብጣቦች አቁመው ነበር።

እንዲሁም ደግሞ ሌሎች ሰዎችን አየሁ፥ በተለያዩ አቢያተክርስቲያኖች ለእሁድ አገልግሎት ሲገኙ። የነጫጮቹ ነጠብጣቦች ዝናብ የመጀመሪያዎቹ የቤተክርስቲያን መጪዎች የቤተክርስቲያኑን ቅጥር እንደረገጡ መውረድ ይጀምራሉ። ለተወሰነ ጊዜ መዝነቡን ቀጠለና ከዚያ አቆመ። አርፋጆች ምንም አያገኙም።

ኢየሱስ እነዚህ ነገሮች ምን እንደሆኑ ተረድቻቸው እንደሆነ ጠየቀኝ እና እኔም እንዳልገባኝ መለስሁለት። ከዚያም አስረዳኝ፡ "*እነዚህ ራእዮች ማለት በተወሰነ ሰዓት ልትገኚ በሚገባሽ ቦታዎች ሁሉና በስንት ሰዓት በዚያ ልትገኚ እንደሚገባሽ የምታውቂ ከሆነ፥ ለዚያ የተወሰነ ሰዓት በረከትን የሚያከፋፍሉ መላእክት አሉ። በሰዓቱ ከደረስሽ በረከትን ትወስጃለሽ አለበለዚያ ግን በረከትሽን ታጫለሽ ምክንያቱም መላእክቱ ለተወሰነ ሰዓት ብቻ ነው በረከቱን የሚያከፋፍሉት። ቪክቶሪያ፥ ላስጠነቅቅሽ እፈልጋለሁ ምክንያቱም ወደ ሥራ ስትሄጂ አርፍደሽ ነው በተለይ ደግሞ ወደ ቤተክርስቲያን ጉባኤዎች (አገልግሎቶች) ስትሄጂ አርፍደሽ ነው። ይህን ልታውቂ ይገባል፥ ያለምንም አሳማኝ ምክንያት ያረፈድሽባቸው በእነዚያ ቀናት፤ ለእነዚያ ቀናት በረከትሽን ለዘላለም አጥተሺዋል፤ መቼም ወዳንቺ አይመለሱም። ቪክቶሪያ ይህን ነገር ልታቆሚና ፈጽሞ ደግመሽ ልታደርጊው አይገባም፥ ለማርፈድ በቂ ምክንያት ካልኖረሽ በስተቀር።*"

ጌታ እነዚህን ቃላት ሲናገር ብሰወር ወይም ስለምግባረ ጎደሎነቴ በቂ ምክንያት ልሰጠው ተመኘሁ። አንዳንዴ ብዙ ስለምተኛ ነው አልሁት ግን ፊትለፊት ዓይን ዓይኔን እያየ እየዋሸሁ እንደሆነ ነገረኝ እናም ከነቃሁ በኋላ ተመልሶ የመተኛት አጉል ልማድ እንዳለብኝ ነገረኝ 'ለጥቂት ተጨማሪ ደቂቃዎች' እንቅልፍን ለማጣጣም በመፈለግ።

ኢየሱስ ካስጠነቀቀኝ በኋላ፥ "*ተነሽ። ነይ እንሂድ። ምክንያቱም ጊዜው ፈጥኖ እያለቀ ነው እናም ልናደርጋቸው የሚገቡን አንዳንድ ነገሮች አሉ።*" አለኝ።

በዚህ ጊዜ ጌታ ፈጽሞ ሆኜበት የማላውቀው ቦታ ወሰደኝ፤ እንዲሁም በዚያ ቀን በሄድንበት መንገድ የሄድነው ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። በተዋቡ አበቦችና በተዋቡ አረንጓዴ ዛፎች የተሞላ ግቢ ደረስን፤ በምድር ላይ ያለ ምንም ነገር ይህን ውበት ሊወዳደረው አይችልም። አበባዎቹ በሁሉም ዓይነት የተዋቡ፥ ደማቅ ቀለሞች ተሞልተዋል። በሚያምር የመናፈሻ ወንበር ላይ ተቀመጥን፥ በድፍን ወርቅ የተሠራ ነበር ትናንሽ ደመቅ ብለው የሚያንጸባርቁ የብር ኮከቦችም ነበሩበት።

ስንቀመጥ፥ ወደ ፊትለፊታችን ጠቁሞ እንዲህ አለ፡ “*ቪክቶሪያ፥ ተመልከች፥ ያ ከተማ ይታይሻል?*” ስመለከት፥ በጣም ትልቅ፥ ደምቆ የሚያበራ ከተማ አየሁ። ከአገላለጽ በላይ የተዋበ ነበር። ከተማው ደማቅ የሚያንጸባርቅ የወርቅ በር አለው እናም በሩ ጋር አንድ ሰው ተቀምጧል፥ እድሜውም ትልቅ ነው። ረዥም ነጭ ጺምና ነጭ ጸጉር አለው። ይህን ሰው አስቀድሜ አይቸው ነበር እናም **ኢየሱስን** ይህ ሰው ማን እንደሆነ ስጠይቀው፥ አብርሃም፥ የእምነት አባት መሆኑን ነገረኝ።

በከተማዋ ውስጥ ብዙ መንገዶችን አየሁ፥ እነርሱም በወርቅ የተለበጡ ናቸው። ረዣዥም ሕንጻዎች አሉ እና እነርሱም እንደ ወርቅ ያንጸባርቃሉ። በከተማዋ ውስጥ የሚታየው ማንጸባረቅና ብልጭልጭታ የማይገለጽ ነው።

**ኢየሱስ** ወደ እኔ ዞወር አለና፥“*ስለዚያ ከተማ ምን ታስቢያለሽ?*” ብሎ ጠየቀኝ።

በጣም እንደሚያምርና ወደዚያ ቦታ መሄድ እንደምፈልግ መለስሁለት። **ኢየሱስም** አለ፡ “***ታዛዥ መሆንሽን ከቀጠልሽ ወደዚያ ወስድሻለሁ ምክንያቱም ቤትሽም በዚያ ነው የሚሆነው። ታዛዥ እንደሆንሽ ቆዪ - ምክንያቱም የማትታዘዢ ከሆንሽ፥ ቪክቶሪያ፥ በቤትሽ ውስጥ ቁራዎች ይበራሉ። ቤትሽ ጉጉቶች(ወፍ) መኖሪያና የመናፍስት መጫወቻ ይሆናል። ሆኖም ግን፥ አትፍሪ፥ ምክንያቱም እኔ ከአንቺ ጋር ነኝ። ብቻ ታዘዢ። ለማይታዘዝ ሁሉ፥ በቤቱ ውስጥ ቁራዎች በዚያ ይበራሉ፤ የጉጉቶች መኖሪያና የመናፍስት መጫወቻ ቦታ ይሆናል።***”

**ኢየሱስ ክርስቶስ** እውነት ነው ሊብራራም በማይችል ፍቅር ይወደናል። ታላቅ ፍላጎቱ ሕይወትን እንድንመርጥና ዘላለማዊ ሕይወትን **ከእርሱ** ጋር እንድናሳልፍ ነው። ያቀረበላቸውን ድኅነት ባለመቀበላቸውና ሞትን በምመረጣቸው ምክንያት ስለሚሞቱትና ወደ ሲያል ስለሚወርዱት ሁሉ ልቡ ይታመማል።

ዳግም የተወለዳችሁ ክርስቲያኖች ብትሆኑም ባትሆኑም፥ እባካችሁ ይህን አንድ ነገር ለሁልጊዜም አስታውሱ፡

# ጊዜው ፈጥኖ እያለቀ ነው።

### ተጨማሪ ጥቅሶች

ራእይ 22:12 እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።

2ኛ ጴጥሮስ 3:9 ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።

ራእይ 3:3 እንግዲህ እንዴት እንደ ተቀበልህና እንደ ሰማህ አስብ፥ ጠብቀውም ንስሐም ግባ። እንግዲያስ ባትነቃ እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ በማናቸውም ሰዓት እንድመጣብህ ከቶ አታውቅም።

የጌታችን የመድኃኒታችንና የንጉሣችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በማቴዎስ 24:27 መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፤

የጌታችን የመድኃኒታችንና የንጉሣችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በዮሐንስ 15:1-3 እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ ነው። ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል።

የጌታችን የመድኃኒታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በማቴዎስ 7:13-14፤ 21፤ 24-29 በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው። በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን

በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፥በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም። ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፥ወደቀም፥አወዳደቁም ታላቅ ሆነ።

ወደ ቆላስይስ 3:5-17 እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ሁሉ ግደሉ፥እነዚህም ዝሙትና ርኩሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣዖትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው፤ በእነዚህም ጠንቅ የእግዚአብሔር ቁጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ ይመጣል፤ እናንተም ደግሞ ትኖሩባቸው በነበራችሁ ጊዜ፥በፊት በእነዚህ ተመላለሳችሁ። አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቁጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ከአፋችሁም ስድብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ፤ እርስ በርሳችሁም ውሸት አትነጋገሩ፥አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል፤ በዚያም የግሪክ ሰው አይሁዳዊም የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም እስኩቴስም ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም፤ ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉ ነው፥በሁሉም ነው። እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ ምሕረትን፥ርኅራኄን፥ቸርነትን፥ትሕትናን፥የዋህነትን፥ትዕግሥትን አድርጉ፥ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ፤ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፤ በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት። በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ፤ የምታመሰግኑም ሁኑ። የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ፥በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት።

ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ብቸኛው አዳኝ፥የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ የእግዚአብሔር አብ ቃል የናዝሬቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በራእይ 21:6-8 እንዲህ አለ አልፋና ዖሜጋ፥መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ። ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል። ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞችም የአስማተኞችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛ ሞት ነው።

ዘሌዋውያን 19:2 ለእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ እንዲህ ባላቸው። እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ።

1ኛ ጴጥሮስ 1:15-16 ዳሩ ግን፦ እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ። (ዮሐንስ 14:1-7፤ ወደ ገላትያ 5:16-26፤ 1ኛ ዮሐንስ፤ ማቴዎስ 24-25፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 4-5)

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥አሜን።
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com